# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 161 ሰኔ 9 2003 ገጽ 1

**መለስ ዜናዊና ባልደረቦቹ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከሃገር ማሸሻቸው የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ባጋለጠ የሳምንታት ጊዜ ውስጥ መሆኑ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ዓይነት ሆኗል። በ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር 50, 000 የጤና ጣቢያዎችን ወይም 150, 000 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሥራት ይቻል ነበር።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-

## በፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ሳንባ የሚተነፍሰው የወያኔ ፓርላማ ግንቦት7ትን ጨምሮ ሌሎች ሶስት ድርጅቶችን በአሸባሪነት ፈረጀ

በፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ሳንባ የሚተነፍሰው የወያኔ ፓርላማ ከትናንትና በስቲያ ማክሰኞ ባደረገው የሸንጎ ስብሰባ የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን፣ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባርንና ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን፤ በሽብርተኝነት መፈረጁን በአገዛዙ ሥር የሚገኘው መገናኛ ብዙሃን ይፋ አድርገዋል።

በሽብርተኝነት የተፈረጁት የኦሮሞ ነጻነት ግንባርና የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር የተከሰሱት፤ መለስ ዜናዊ እራሱ የሚመራው ህዝባዊ ወያኔ ሃሪነት ትግራይ በአማርኛ አጠራሩ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር በ17 አመት ጸረ ደርግ የትጥቅ ትግል ወቅት በተጠቀመባቸው የትግል ስልቶች በመጠቀማቸው እንደሆነ ያተተው የውሳኔ ሰነድ የህወሃትን አላማና የትግል ሥልት በመቃወማቸው ብቻ በነመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በፍጹም አረሜኔያዊነት ስለተጨፈጨፉት ከ30 ሺህ በላይ የትግራይ ወጣቶች ፤ በህወሃት ታጋዮች ስለፈረሱት ድልድዮች፤ ትምህርት ቤቶች ፤ ጤና ጣቢያዎች፤ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋሞች፤ የልማት ድርጅቶች፤ ስለተዘረፉት ባንኮች ወዘተ ህዝብ ግንዛቤ እንደሌለው ታሳቢ የሚያደርግ መስሎ ቀርቦአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አሜሪካ ስለዲሞክራሲ እየደሰኮሩ የህዝባቸውን ስቃይ የሚያራዝሚ የአፍሪካ አምባገነኖች የተሳሳተ የታሪክ ምዕራፍ ላይ መሆናቸውን ሂላሪ ክሊንተን በአዲስ አበባው ግቡኝታቸው ወቅት ገለጹ

ባለፈው ሰኞ የአፍሪካ ጉብኝት አድርገው ወደአገራቸው የተመለሱት የአሜሪካ ውጪ ጉዳይ ሚንስትር ሚ ስ ሂላሪ ክሊንተን በአዲስ አበባ ጉብኝታቸው ወቅት በአፍሪካ ህብረት ጽ|ቤት ተገኝተው ባደረጉት ንግግር ህዝባቸውን እያሰቃዩ ለአመታት ስልጣን ላይ እየቆዩ ያሉት የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች መለወጥ እንዳለባቸዉ በግልጽ ተናገሩ።

የበርካታ አፍሪካ መንግሥታት ተወካዮች በተሰበሰቡበት ንግግር ያደረጉት ሚስ ሂላሪ ክሊንተን ያለህዝብ ፍላጎት ለረጂም ጊዜ ስልጣን ላይ የቆዩ እና የዲሞክራሲ ለዉጥ ለማድረግ ፈቃደኛ የማይሆኑ የአፍሪቃ አምባገነን መሪዎች ተቀባይነት እንደሌላቸዉና በተሳሳተ የታሪክ ምዕራፍ ላይ መሆናቸውን ከፍተኛ አጽንኦት ሰጥተው እንደተናገሩ የዋሽንግተን ፖስት ባለፈው ሰኞ እትሙ ገልጾአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በቤልጂዬም የሚገኘው የወያኔ አምባሳደር ካሱ ኢላላ የተባባሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጣውን የ$8 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር በህገወጥ መንግድ ከአገር መውጣት ዜና አልሰማሁም አለ

ወያኔ አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ማግሥት መለስ ዜናዊን ለማጀብ የማይወክለዉን የጉራጌን ብሔረሰብ እወክላለሁ በማለት በሽግግሩ መንግስት ዉስጥ የኢህዴዴግ አባል በመሆን በመጀመሪያ የመለስ ዜናዊ አማካሪ ከዚያ የመሰረተ ልማት ሚንስቴር በመቀጠልም የከተማ ልማት ሚንስቴር በመሆን ያገለገለዉና በቅርቡ ለመለስ ዜናዊ ባለዉ ታማኝነት በቤልጂዬም የወያኔ አምባሳደር ሆኖ የተሾመው ካሱ ኢላላ ባለፈው ቅዳሜ ሰኔ 4 ቀን ብራስልስ ዉስጥ በጠራው ስብሰባ ላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በህገ ወጥ መንገድ ከአገር ወጥቶ በውጭ አገር ተከማችቷል ስላለው $8 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉዳይ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ መናገሩን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከብራስልስ በላከልን ዜና አስታወቀ።

የወያኔ አገዛዝ ባለፉት ሃያ አመታት ኢትዮአጵያ ዉስጥ አስመዘገብኩት የሚለውን መልካም አስተዳደር፤ ዲሞክራሲና የልማት ስራ በመተንተን የስብሰባውን አብዛኛውን ጊዜ የወሰደው ካሱ ኢላላ የመለስ ዜናዊ አስተዳደር በሚቀጥሉት አምስት አመታት አከናውናለሁ በማለት ያቀደውን የልማትና ትራንስፎርመሽን መረሃግብር ቁጥራቸው ከ70 ለማይበልጡ የስብሰባው ተሳታፊዎች ለማስረዳት ሙከራ አድርጓል። የግንቦት 7 ዘጋቢ ከብራሰልስ እንደዘገበዉ በስብሰባው ላይ የተገኙት ሰዎች አብዛኛዎቹ በዘር፤ በቋንቋና በግዜያዊ ጥቅም ገዢዉን ፓርቲ የተጠጉና አገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን አስከፊ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች መረዳት እንዳይችሉ ወያኔ ፊታቸዉን በገንዘብ የሸፈናቸዉ የኢኮኖሚ ጥገኞች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል። ወያኔ በአገር ቤት እንደሚያደርገው ሁሉ በውጪው አለም ሚገኙትን ተቃዋሚ ኃይሎች ለማዳከም የፖለቲካ ንቃታቸው ዝቅተኛ የሆኑትን ስደተኞች በአነስተኛ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል ማሰማራት ጀምሯል ያለው ዘጋቢያችን፤ ካሱ ኢላላ በጠራው በቅዳሜው ስብሰባ ላይ የወያኔን አገዛዝ በመተቸት አስተያየታቸውን ለመስጠት የሞከሩ ግለሰቦች የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ እንዳይጠቀሙ ሲያደናቅፉ መድረኩን የሚመሩት የኤምባሲው ሹመኞች በኩራትና በደስታ ሲወጠሩ ተስተውለዋል ብሏል።

የካሱ ኢላላ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዲስኩር ያልጣመው አንድ ወጣት UNDP ማለትም የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም መለስ ዜናዊና ሃይለማሪያም ደሳለኝ በተሳተፉበት የኢስታንቡል ስብሰባ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በወሎ ዩኒቨርሲት ተማሪ የሆኑ 14 የሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮች በወያኔ ጸጥታ ሠራተኞች እንደታፈኑና ሰቆቃ እንደተፈጸመባቸው ታወቀ

ቁጥራቸው 14 የሚሆን በወሎ ዩኒቨርሲቲ የኮምቦልቻና የደሴ ካምፓስ የ2ኛና 3ኛ አመት ሴት ተማሪዎች ባልታወቀ ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው ላይ በጸጥታ ሠራተኞች ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ ለተወሰኑ ቀናት የደረሱበት ቦታ ሳይታወቅ ከቆየ በኋላ 8ቱ ተማሪዎች በከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ሲለቀቁ 6ቱ በሌሊት ወደ አዲስ አበባ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ተወስደው ከፈተኛ ምርመራ ሲደረግባቸው እንደሰነበተ ለተማሪዎቹ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ።

እንደመረጃ ምንጫችን ሪፖርት ከወራት በፊት 6 የኮምቦልቻ ግቢ ተማሪዎች የሃይማኖታቸው ህግ በሚፈቅደው መሠረት ለብሰው በመታየታቸው የትምህርት ቤቱን ደንብ ጥሳችኋል በሚል ተወንጅለው ለሁለት አመት ከትምህርታቸው እንደታገዱና በተመሳሳይ ምክንያት የተከሰሱ 8 ሌሎች የደሴ ግቢ ሴት ተማሪዎች ደግሞ የሁለት አመት እገዳ እንደተጣለባቸው ለማወቅ ተችሏል። የተማሪዎቹን ህገመንግሥታዊ መብት ተጋፍቷል በተባለው በዚህ የሥነሥረአት እርምጃ ቅር የተሰኘው የእስልምና ጉዳዮች ጸህፈት ቤት ዋና ጸሃፊውን አልሙሃመድ ስራጂን ወደስፍራው ልኮ ከዩኒቨርሲቲው ባለሥልጣናት ጋር ከተወያየ በኋላ በተማሪዎቹ ላይ የተላለፈው የሁለት አመት እገዳ እንዲነሳላቸው በተደረገ በአስረኛው ቀን ሰኔ 1 ቀን 2003 እድሜያቸው በ19ና በ21 አመት መካከል የሚገኙ 6 ሴት ተማሪዎች ታፍነው ወደ ማዕከላዊ ምርመራ ተወስደዋል። በኢሰብዓዊነቱ፤ በጭካኔዉና በሰቆቃ አድራሽነቱ ወደሚታወቀው ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ የተወሰዱት ተማሪዎች

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን በበላይነት የምትመራው የኤች አይ ቪ ኤድስ መከለከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት በሽታውን ለመከላከል ተብሎ በእርዳታ የሚሰጠውን ገንዘብ ወደ አልታወቀ ቦታ እንዲተላለፍ እንደሚያደርግ ተጋለጠ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ቢሮ ዋና ኦዲተር ለተወካዮች ምክር ቤት ተብዬው የወያኔ ሸንጎ ባቀረበው ሪፖርት ሪፖርት እንደገለዉ፣ ቢሮው ባካሔደው የኦዲት ምርመራ በ16 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ 1.45 ቢሊዮን ብር በላይ ከተፈቀደለት ተግባር ውጪ አድራሻው ወደአልተገለጸ ቦታ ማዛወሩን አጋልጦአል። ዋና ኦዲተሩ ገንዘቡ ወደ ወደአልታወቀ ቦታ ተዛውሮአል በማለት ድፍንፍን ያለ ሪፖርት ያቀረበበት ዋናው ምክንያት የመለስ ዜናዊ ባለቤት የሆነቿውንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሙስና እመቤት የሚል ተቀጢላ በህብረተሰቡ የተሰጣትን አዘብ መስፍንን ማጋለጥ ስለፈራ እንደሆነና ገንዘቡ ከርሷ በተሰጠ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ወደ ግል ካዚና ሳይዞር እንዳልቀረ የሂሳብ ባለሙያዎች ጥርጣሬያቸውን መግለጽ ጀምሮዋል።

የዋናው ኦዲተር ወደ ሌላ ቦታ ዞሮአል በማለት በድፍኑ ካስቀመጠው ገንዘብ መጠን በተጨማሪ በአሜሪካ መንግስት ከሚመራው ግሎባል ፈንድ ተገኝቶ ለአስፈጻሚ አካላት ተሰጥቶ ሳይወራረድ የቆየ በድምሩ 752 ሚሊዮን 420 ሺ 349 ብር መኖሩንና ከዚህ ውስጥ በድምሩ 624 ሚሊዮን 324 ሺ 142 የሚሆነውን ያልተወራረደ ገንዘብ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በስሩ ያሉ መስሪያ ቤቶች የያዙ መሆናቸዉ ተጠቅሷል። በአገር አቀፍ ደረጃ ከፌዴራል ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈትቤት ወጪ በሆነ ገንዘብ የተዘጋጀዉ የገቢ ማስገኛ፣ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በ2002 የበጀት አመት ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ያለህጋዊ መረጃ መመዝበሩ ታወቀ

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ከትናንት በስቲያ ለምክር ቤት ባቀረበዉ የ2002 በጀት አፈፃፀም ዘገባ፤ የሂሳብ ምርመራ ካደረገባቸዉ 40 ያህል መስሪያ ቤቶች፤ በአብዛኞቹ ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት መመልከቱን በተጨማሪም ከደንብና መመሪያ ዉጭ በመስራት የአገር ሃብት ያለአግባብ እየባከነ እንደሆነ ማስታወቁን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በ16 መ|ቤቶች ብቻ ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ህጋዊ ደረሰኞች ሳይቀርቡበት ወጪ ሆኖአል፤ 887.49 ሚሊዮን የሚሆን ደግሞ ዉዝፍ ያልተወራረደ ሰነድ መገኘቱና ከዚህም ዉስጥ 340.9 ሚሊዮን በትምህርት ሚኒስቴር ዉስጥ እንደተገኘ ለማወቅ ተችሏል።

ከዚሁ ዘገባ ጋር በተያያዘ ለዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቅርበት እንዳለው የሚነገርለት ሪፖርተር ጋዜጣ ዋናው ኦዲተር የፓርላማ አባላትን ያስጨበጨበ ሪፖርት አቀረበ የሚል አስቂኝ ዜና መዘገቡን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጿል።

የገንዘብ ምዝበራውንና ሪፖርተር ጋዜጣ የሰጠዉን ዘገባ አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ሰራተኛ እንደገለጹት ለኔ የዚህ ገንዘብ ምዝበራ ሪፖርት የሚደንቀኝም የሚያስገርመኝም አይደለም። ምክንያቱም ይህ በምርመራ ተደረሰበት የተባለው ምዝበራ በትክክል ከተፈጸመው ምዝበራ እጅግ በጣም ያነሰ ስለሆነ ነዉ ብለዋል። በማያያዝም ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ውስጥ "የአሳ ግማቱ ካናቱ" እንዲሉ መለስና ባለቤቱን ጨምሮ በወያኔ አገዛዝ ዙሪያ የተኮለኮሉ ባለስልጣናት በጠራራ ፀሐይና ባደባባይ ልክ የሌለዉ ገንዘብ እየዘረፉ ባለበት ሁኔታ ይህ በመስሪያ ቤቶች ዉስጥ ተገኘ የሚባለዉ ምዝበራ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ታንኮች ፍርሃትን አይሸፍኑም፤ ህዝባዊ አመጽን አያስቀሩም!

አምባነገኑ መለስ ዜናዊ "እያንዳንዷን ሳንቲም ቆጥበን ለአባይ ግድብ ሥራ እናውላታለን" ባለ ጥቂት ወራት ውስጥ በአንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪ ሁለት መቶ ታንኮችን ከዩክሬን መግዛቱ ዓለም ዓቀፍ የዜና አውታሮች ይፋ አድርገዋል። ከኮሚኒዝም መወደቅ በኋላ ይህ ለዩክሬን ትልቁ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ኮንትራት ነው ተብሏል።

ይህ ዜና የተሰማው መለስ ዜናዊና ባልደረቦቹ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከሃገር ማሸሻቸው የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ባጋለጠ የሳምንታት ጊዜ ውስጥ መሆኑ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ዓይነት ሆኗል። በ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር 50, 000 የጤና ጣቢያዎችን ወይም 150, 000 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሠራት ይቻል ነበር። ይህን ያህል የሃገር ሃብት መመዝበሩ እያንገበገበን ባለበት ወቅት የ100 ሚሊዮን ዶላር ታንክ ግዥ ዜና ተጨመረበት።

ለመሆኑ 100 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ምንያህል ነው? ይህ ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር ከ 17 ቢሊዮን ብር (ብር 17, 000,000,000.00) በላይ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ለታንኮቹ የወጣው ገንዘብ 17, 000 የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ወይም ወደ 5, 500 የሚጠጉ የጤና ጣቢያዎችን መገንባት ይቻል ነበር። መለስ ዜናዊ ግን ከት/ቤትና ጤና ጣቢያ ይልቅ ታንኮች ገዝቶ መታቀፍን መርጧል።

ለመሆኑ መለስ ዜናዊ ታንኮችን የገዛው ለምድነው? ለማነው?

መለስ በአሁኑ ሰዓት ዘመናዊ ታንኮችን ለመግዛትና ለመታጠቅ የፈለገው በሚከተሉት ሁለት ተቃራኒ ምክንያቶች ነው ብለን እናምናለን።

**1. ፍርሃት**

መለስ የፍርሃት ቆፈን ውስጥ ነው። መለስ የሚፈራው የኢትዮጵያን ህዝብ ነው። በምርጫ 97 ማግስት የመለስ ዜናዊ ታንኮች በከተማ ውስጥ ህፃናትን ሲያሸብሩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ ሲቪሉን ማኅበረሰብ በማሸበር ሥልጣኔን እከላከላለሁ ብሎ ተስፋ አድርጎ ሊሆን ይችላል። ለዚህ መላምት ተጨማሪ ማስረጃ የሚሆነን በምርጫ 97 ማግስት የአዲስ አበባን ህዝብ በጦር አይሮፕላኖች ለማሸበር ተሞክሮ በአብራሪዎቹ አለመተባበር ከሸፎ የነበረ በመሆኑ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያለ ሰው የሚበሩ የጦር አይሮፕላኖችን ከእስራኤል መግዛቱ ነው።

**2. የሰፈር ጉልቤ የመሆን ህልም**

የመለስ ፍርሃት እንዳለ ሆኖ የአፍሪቃ ቀንድ ኃያል ገዢ የመሆን ቅዠትም ይኖረዋል ብለን እናምናለን። የአፍሪቃ ቀንድ በከፍተኛ ሁኔታ እየተቀየረ ያለ ቀጠና ነው። ግብጽ መሠረታዊ በሆነ የለውጥ ሂደት ውስጥ ነች። ሱዳን ተከፍላ አዲስ አገር ተፈጥራለች። ይህ በመሆኑ ግን የሱዳን የውስጥ ችግሮች እየተቃለሉ አይደሉም። የመንም ከግብጽ ባላነሰ የለውጥ ሂደት ውስጥ ነች። ሶማሊያ ከተዘፈቀችበት ማጥ በቅርቡ የምትወጣ አይመስልም። መለስ ከዚህ የለውጥ ሂደት እተርፋለሁ ብቻ ሳይሆን አተርፋለሁም ብሎ ሊቃዥ ይችላል።

ከላይ የሰፈሩት ሁለት ምክንያቶች ተቃራኒዎችና አንዳቸው ሌላኛውም የሚያፈርሱ ቢመስሉም በተግባር ግን አብረው ሊታዩ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። አብዛኛዉን ጊዜ አምባነኖችን መሳሪያ የሚያስገዛቸው፤ የጎረቤት አገርን የሚያስወርራቸው ፍርሃታቸው ነው። ሥር የሰደደ ፍርሃታቸውን በውሸት ጡንቻ ለመደበቅ ይጥራሉ። መለስም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው።

ሆኖም ግን የተደራጀ የጦር ሠራዊት መኖር አምባገነኖችን አላዳናቸውም፤ ወደፊትም አያድናቸውም።

ሩቅ ሳንሄድ:-

- በአፍሪቃ በወታደራዊ ብቃት የመሪነት ደረጃ ላይ ያለ ሠራዊት መገንባቱ ሙባረክን አላደነውም፣
- እንደ ፈጣሪ የሚያመልኩት ጄኔራሎች መመልመሉ፤ ከፍተኛ የአዛዥነት ቦታዎችን በልጆቹና በቅርብ የሥጋ ዘመዶቹ ማስያዙ ጋዳፊን ከህዝባዊ ማዕበል አላዳነውም። ጠብመንጃ ነክተው የማያውቁ የነበሩ ሊቢያውያን ሲቪሎች ስድስት ወራት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በጎበዝ አለቃ ተደራጅተው የጋዳፊ ልጆችና ዘመዶች የሚመሩትን ጦር እያርበደበዱ ነው፣
- በየመንም አሊ አብደላ ሳልህ ሰራዊቱን በጎሳ ማደራጀቱ አልጠቀመውም። የራሱ ጎሳ አባላትም ሳይቀር ሰዎች ናቸውና ነፃነት ፈልገው በራሱ ላይ አምፀውበታል።

ተመሳሳይ ክስተት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚደገም በበኩላችን ጥርጣሬ የለንም።

ስለሆነም ከዩክሬን የተገዙ 200 ታንኮችም ሆነ ከእስራኤል የተገዙት ያለ ሰው የሚበሩ የጦር አይሮፕላኖች ለነፃነት የምናደርገውን ትግል ሊያደናቅፉ ቀርቶ በትንሹ እንኳን ሊያዘገዩት አይቻላቸውም። እንዲያውም የታንኮቹ መገዛት የመለስን ፍርሃት አጉልተው ስለሚያሳዩን ብርታትን ይጨምሩልናል።

ነፃነት የናፈቀው ህዝብ አምርሮ የተነሳ እለት የሚያቆመው ኃይል አይኖርም። ያንን ቀን ለማቅረብ ጠንክረን እንስራ። "ባርነት፣ ድህነት፣ አድልዎ በቃን!" እንበል።

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

---

### በፉሽስቱ መለስ ዜናዊ ሳንባ የሚተነፍሰው የወያኔ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከሳምንታት በፊት "ግንቦት 7 በውስጣችን ሳይቀር ኩይሳውን ሰርቶ እየቦረቦረን ነው" በማለት የተናገረው መለስ ዜናዊ ግንቦት 7ን ጨምሮ ሶስቱን ድርጅቶች በሽብርተኝነት ለማስፈረጅ የፈለገው የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ከመሰረቱ ነቅሎ ለመጣል ሶስቱም ድርጅቶች በጋራ ለመስራት ወደሚያስችላቸው ምዕራፍ እየተሸጋገሩ መሆኑ አስበርግጎት እንደሆነ ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው ምንጮች አዲስ አበባ ለሚገኘው ዜጋቢያችን ገልጸዋል።

ወያኔ የህዝብ ተወካዮች የሚላቸው እንጀራ ፈላጊዎች አጸደቁት በተባለው ድርጅቶቹን በሽብርተኝነት የፈረጀ ሰነድ ላይ "ግንቦት 7 በቀድሞ የቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች የተቋቋመ ድርጅት ነው" ካለ ቦኋላ "እነኚህ አመራሮች ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ መሞከራቸው በፍ/ቤት ተረጋግጦና አምነው በድርጊታቸው ተጸጽተው ከእንግዲህ ወዲያ ህገ መንግስቱን እንደሚያከብሩና እንደሚያስከበሩ ቃል ገብተው ይቅርታ ይደረግላቸው ዘንድ መንግስትና ህዝብ በይፋ በመጠየቃቸው ይቅርታ ተደርጎላቸው ከእስር እንዲፈቱ መደረጉ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በይቅርታ ከእስር ከተፈቱ በኃላ ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በማናቸውም መንገድ ለማፍረስ አቅዶ የሚንቀሳቀስ ግንቦት 7 የሚል ቡድን ወይም ድርጅት አቋቋሙ፡፡ ብሎአል።

በመቀጠልም "ድርጅቱ ዓላማዬ ብሎ በይፋ ያወጀው "ሁሉን አቀፍ ትግል" በመጠቀም አሁን ያለውን መንግስታዊ ሥርዓት ማፍረስ ሲሆን በተለይ ደግሞ በከተሞች አካባቢ በመሰረተ ልማት ተቋማት ፣ በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ ሽብርና ግድያ መፈጸም እንዲሁም የከተማ አመጽ ማቀጣጠል የትጥቅ ትግል ማካሄድ እና ከማናቸውም ጸረ ኢትዮጵያ መንግስት አቋም ካላቸው ድርጅቶችና ሀገሮች ጋር በጋራ መስራት ነው"፡ በማለት የግንቦት7 መፈጠር ያሳደረበትን ስጋትና ጭንቀት ገልጾአል፡፡

የፌደራል ጉዳዮች ሚንስቴርና የመለስ ዜናዊ አማካሪ የሆነው አባጸሃይ ከወራት በፊት ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ጋር የሰላምና የእርቅ ስምምነት ተፈርሞአል ፤ በዚህም ምክንያት ከአሁን ቦኋላ ኦብነግ የሚባል ድርጅት የለም በማለት ለህዝብ ተወካዮች ተብዬው ምክር ቤት ሪፖርት አቀርቦ እንዳልተጨበጨበ በራሳቸው አንደበት ገድለው የቀበሩትን ድርጅት ከመቃብር አስነስተው " ለብሄራዊ ጸጥታ አስጊ በመሆኑ በሽብርተኝነት ፈርጀነዋል " ማለታቸው አገራችን በምን አይነት ሂሊና ብሶች ስብስብ እየተመራች እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ሆኖአል።

የንቅናቄያችን የህዝብ ግንኙነት የወያኔ ምክር ቤት ስላስተላለፈው ስለዚህ ውሳኔ ከድርጅቱ የተሰጠ ይፋዊ ምላሽ ካለ እንዲያካፍለን ተጠይቆ፤ በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ አገሮች እንደተመለከትነው፤ ስልጣንን የሙጥኝ ብለው ህዝባቸውን እየገደሉና እየመዘበሩ የአገዛዝ ዕድሜያቸውን ለማራዘም ለአመታት የተለያየ አፋኝ ደንቦችን በማውጣት በህዝብ ላይ ለመጫን የሞከሩት ከዚያም አልፈው በሚሊዮን የሚቆጠር የወታደራዊና የደህንነት ሃይል ገንብተው የኖሩት ህዝብ በቃኝ ብሎ የተነሳ እለት እሳት እንደነካው የገለባ ክምር ወዲያው ከመጥፋት እንዳላዳናቸው በአይናችን እየተመለከትን ስለሆነ የመለስ ዜናዊ ዕጣ ፈንታም ይህ ሊሆን እንደሚችል ስለሚገባን ለነርሱ ፋይዳ ቢስ ውሳኔ በንቅናቄያችን ሥር በሚተዳደሩ ሚዲያዎች በተለይም በሳምንት ሶስት ቀን ብቻ በሚተላለፈው የሬዲዮ ፕሮግራማችን አጣዳፊ ምላሽ ለመስጠት ተብሎ ያለቺንን አጭር የሥርጭት ጊዜ መሻማት አላስፈለገንም ብለዋል።

### በወሎ ዩኒቨርሲት ተማሪ የሆኑ 14 የሙስሊም . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

1ኛ/ ተማሪ ነኢማ ይመር የ3ኛ አመት የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ተማሪ፤
2ኛ/ ተማሪ ሃያት መሃመድ ከባህርዳር የመጣች የጨርቃጨርቅ ሳይንስ ተማሪ፤
3ኛ/ ዘምዘም መሃመድ
4ኛ/ ዘምዘም አህመድ ሁለቱም የ3ኛ አመት የሂሳብ ተማሪዎች፤
5ኛ/ ተማሪ ፋጡማ መሃመድ ከአፋር ክልል የመጣች የኤሌክቲሪካል ኢንጂኔሪንግ ተማሪና
6ኛ/ ተማሪ ሃዲያ ነጋ ከአፋር ክልል የ2ኛ አመት ስታቲስቲክስ ተማሪዎች መሆናቸው ታውቋል።

ወደ ኮምቦልቻ ማዘጋጃ ቤት ተወስደው የተለቀቁት ተማሪዎች መታሰራቸውንና በታሰሩበት ወቅት የተፈጸመባቸውን ምርመራ ለማንም ሰው ቢናገሩ ለህይወታቸው የሚያሰጋ እርምጃ እንደሚወሰድባቸው እንደተዛተባቸው ምንጫችን አያያዞ ገልጾአል።

ወያኔ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም አንዱን ብሄር ከሌላው በማጋጨት ገላጋይና ሰላም አስከባሪ መስሎ ለመታየት የሚያደርገው ሴራ ከተነቃበት ወዲህ ተከባብሮና ተቻችሎ የኖሩትን የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶች በማጋጨትና ደም ለማቃባት በተደጋጋሚ ሲሞክር ታይቷል።

### በቤልጂዬም የሚገኘው የወያኔ አምባሳደር ካሱ ኢላላ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ለአለም ህዝብ ይፋ ያደረገውን የ8 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከአገር በህገወጥ መንገድ መውጣት አስመልክቶ ላቀረበው ጥያቄ ካሱ ኢላላ እንዲህ አይነት ሪፖርት መውጣቱን በፍጹም እንዳልሰማ ከተናገረ በኋላ ትንሽ ቆይቶ ሪፖርቱን ያወጣው ድርጅት የተሳሳተ መሆኑን ገልጾ ይቅርታ ጠይቋል እስከማለት መድረሱን በስብሰባው ላይ የተገኘው ሪፖርተራችን ገልጿል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዲሞክራሲ አስፍኛለሁ የሚለው የወያኔ አገዛዝ እሱ ራሱ በፃፈዉ ህገመንግሥት ላይ የሰፈረውን የሃይማኖት ነጻነት ማክበር ተስኖት ሙስሊም ተማሪዎች በተለያዩይ ቦታዎች በአገዛዙ ጸጥታ እንደሚታፈኑ የተገለጸ ሲሆን፤ አገዛዙ በሃይማኖት ተቋሞች ውስጥ ጣልቃ እየገባና የራሱን ፖለቲካ ታማኞች በመሪነት ቦታ ማስቀመጥ ከጀመረ ቆይቷል። እነዚህ አስከፊ ሁኔታዎች በዚህ መልክ እስከቀጠሉ ድረስ ወይም አገራችን ውስጥ ለዲሞክራሲ የቆመ መንግስት እስካልተመሠረተ ድረስ ይህ የሚታወሩት የልማት እቅድም ሆነ ድህነትን የማጥፋት ጥረታችሁ ሁላችንንም የሚያሳትፍ አይደለም በማለት ሃሳብ በማቅረብ ላይ የነበረ አንድ ተሰብሳቢ ንግግሩን በአግባቡ ተናግሮ ሳይጨርስ ዕድሉን እንደተቀማና ፤ አንድ ለሆዱ ያደረ አስተያየት ሰጪ ደግሞ መንግሥትን በማይመለከት መልኩ በሃይማኖቶች መካከል ያለዉን ግጭት ሲናገር የወያኔ ጄሌዎች ሲያጨበጭቡ መስተዋላቸውን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ካሱ ኢላላ አባል በሆነበት የዴህዲግ ምክር ቤት ውስጥ ለግምገማ ቀርቦ በፈጸመው ሙስና ክፉኛ ሲተች "በስብሻለሁ እና መሃሪው ኢህአዴግ ይቅርታ ያደርግልኝ "ብሎ መማጸኑን የወያኔ መገናኛ ብዙሃን በወቅቱ ዘግበው እንደነበርና በዚህም የተነሳ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ "የበሰበሰው" የሚል ቅጽል እንደተሰጠው ይታወቃል።

ካሱ ኢላላ እወክለዋለሁ የሚለው የጉራጌ ድርጅት በ1985 አም አካባቢ ከፓርቲው እንዳባረረውና በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ የዴቡብ ህዝቦች ዲሞክራሲያው ግንባር ውስጥ እንዲቀጥል መደረጉ ይታወሳል።

ሃይለ ሀሳብ
የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 161 ሰኔ 9 2003 ገጽ 3

# የህዝባዊ እምቢተኛነት የነጻነት ትግል በፖለቲካ ድርጅቶች የመመካከርና የመተባበር አጀንዳ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

(ለግንቦት 7 አባላት ለውይይት የቀረበ ጽሁፍ፤ ግንቦት 2003) (ክፍል 3 )

## 5. ያለ ህዝባዊ አንድነት ነጻነት እንደማይኖር የገባው ወጣትና ህዝብ

የሃገራችንም ህዝብ ወያኔን ለማቸነፍ የግድ የትግል አንድነት መፍጠር እንዳለበት ያውቃል። ወያኔን በማሸነፍ የሚቀዳጀውን ድል ለመከላከል አንድነቱን ጠብቆ መሄድ እንደሚገባው የሚስተው አይደለም። የቱኒዝያን የግብጽ ተመክሮ የሚያሳየው ይህንኑ ነው። አሁንም ኢትዮጵያውያን እንደ ግብጾች አርቆ አሳቢ አይደሉም ካላልን በስተቀር። ይህ እውቀት ደግሞ ጠባብ የሆነ የድርጅት አጀንዳዎች የሚያስተናግድበት ሰፊ ሆድ አይኖረውም። የህዝብ የመታገያ ጥያቄዎች ሁሉንም ህዝብ በጋራ ማንቀሳቀስ የሚያስችሉ እንጂ አንዱን ወገን ተቀብሏቸው ሌላው ወገን የኔ አይደሉም የሚላቸው ሊሆኑ አይገባም። አድማሳዊ የሆኑ የመብት፣ የነጻነት፣ የፍትህና የእኩልነት ጥያቄዎች ብቻ ናቸው የሃገሪቱን ህዝብ በአንድነት እንዲጓዝ የሚያደርጉት። ከዚህ ውጭ ሁሉም በየራሱ አጀንዳ እንመራ ካለ የቱንዚያና የግብጽ ህዝብ በአምባገነን መሪዎቹ ላይ የተቀዳጀውን ድል የኢትዮጵያ ህዝብ መቀዳጀት እንደማይችል ያውቃል።

በጣህሪር አደባባይ ቁራንና መስቀልና የያዙ አማኞች ያስተላለፉት መልእክት "ሙባረክንና ጓደኞቹን ማሸነፊያ መሳሪያችን አንድነታችን" ነው የሚል ነበር። ይህ መልእክትና ትርጉሙ በአለም ላይ ከጭቆና ለመውጣት ለሚታገሉ ህዝቦች ደርሷል። ከዚህ መልእክት በፊትም ይህንን ሃቅ ተራ በተራ በወያኔ እየተቀጠቀጠ ያለው ዜጋ በሙሉ ያውቀዋል። የሃገሪቱ ህዝብ ከሌሎች ሃገሮች ልምድ የቀሰመውን ወሳኝ ትምህርትና ራሱም በደመነፍሱ የሚሰማው ስሜት የትግል አንድነት መፍጠር በአምባገኖች ላይ የማያዳግም ድል ለመቀዳጀት ወሳኝ መሳሪያ እንደሆነ ነው።

በኢትዮጵያ ያለው የእምነት ልዩነት ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያ በርካታ የተለያዩ የዘውግ ማህበረሰባት ያሉባት ሃገር ናት። ወያኔ ደግሞ የተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰባትን እርስ በርሳቸው እንዲናከሱ ለማድረግ ያልጠነሰሰውና ያልተገበረው ሴራ የለም። ወያኔን እንቃወማለን የሚሉ ድርጅቶችም በቀጥታ በሰሯቸውና ባልሰሯቸው ስራዎቻቸው ይህን የወያኔን ከፋፍሎ የመግዛት እኩይ ስራና ከዚህ የመከፋፈል ሴራው ያገኘውን የተጋነነ አቅም ማርከስ ሳይችሉ እስካሁን ቆይተዋል።

አሁን ግን ህዝብ ራሱ መከፋፈሉ የባርነት ሰንሰለቱን ማጥበቂያ እና በጥቂቶች የመረገጫና የመዘረፊያ ምክንያት መሆኑን ተረድቷል። "ተለያይተን በማመጽ ወያኔ በተናጠል እንዲመታን እድል አንስጠው። በሁሉም የሃገርቱ ክልል በአንድ ግዜ በአንድ ላይ ተነስተን ወያኔ ምንም ሊያደርገን እንደማይችል እናሳየው። የሁላችንም ስብእና የሚያከብር ለሁላችንም በእኩልነት የሚያይ መብታችን የሚንከባከብ የስርአት ለውጥ እናምጣ" ነው ህዝብ የሚለው። ማህበረሰቦች እንዳይገናኙና ወያኔ የዘረጋውን ዘረኛ የጥቂቶች ስልጣን እንዳይፈታተኑ በማሰብ አገዛዙ ሰብሮት የነበረው ድልድይ ወያኔ በሁሉም ማህበረሰብና ዜጋ ላይ በሚያዘንበው የግፍና የውርደት ጎርፍ የተነሳ ተመልሶ እንዲገነባ የግድ ሆኗል። የዛሬን ፈተና አልፎ ነገ ለልጆቹ የተስፋ ሃገር ማውረስ የሚቻለው ስቃይና ግፍ በቃ ብሎ በአንድነት መነሳት እስከቻለ ድረስ እንደሆነ የሃገሪቱ ህዝብ ከተረዳ ሰንብቷል። የቱኒዝያና የግብጽ አብዮት ያደረገው ነገር ቢኖር ይህ የሃገራችን ህዝብ ግንዛቤ ትክክል እንደሆነ ተጨማሪ ማስረጃ መስጠት ብቻ ነው።

ይህ አንድነት የቆመው የጋራ ሰብአዊ ክብርን ለመቀዳጀት፤ በጋራ ነጻነትን ለመጎናጸፍ፤ በጋራ ከዘረፋና ከድህነት ለመገላገል ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ የሃገሩ ግዛታዊ ወይም ሉአላዊ አንድነት በህዝብ ቁጥጥር ስር የሚውል መንግስት ሳይኖር መረጋገጥ የማይችል እንደሆነ በሚገባ የተረዳ ህዝብ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነናዊ በሆነ መንገደ የግዛት አንድነትን እናስከብራለን በሚል መንገድ ለተጓዙ አገዛዞች ብርቅየ ልጆቹን ገብሮ የተማረው ትምህርት አምባገነናዊ ስርአቶች አንድነት እንደማያስጠብቁ ነው። ልኡላዊ የግዛት አንድነት ሆነ ማህበረሰባዊ አንድነት ከዴሞክራሲ ስርአት ምስረታ ውጭ ሊከበር እንደማይቻል የሚያውቅ ህዝብ ቅድሚያ በዜጎች አንድነት ላይ ለቆመና ለዴሞክራሲ የሚደረግ ትግል መስጠቱ ትክክልና ተገቢ ነው።

ግልጽ የሆነ የአንድነትና የዴሞክራሲን ችግሮች ሊፈታ የሚችል የትግል ሂደት በሃገር ወስጥና ከሃገር ወጭ መልክ እያያዘ እየመጣ ነው። በፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች አካባቢ ካለው በጋራ የመስራት ፍላጎት በላቀ ደረጃ የተለያዩ ብሄርና ብሄረሰብ አባላትና ማህበረሰባቸው በአንድነት ለመስራት በስሜት የሚንቀሳቀሱት የማህበረሰቦችና የዜጎች አንድነት የነጻነት ምንጭ መሆኑን በሚገባ በመረዳታቸው ነው። የኦሮሚያ ወጣቶች የሃገሪቱን ህዝብ በሙሉ ስቃይና በደል የሚገልጹ ጥያቄዎች አንስተው በጋራ እንታገል የሚል ጥሪ ሲያቀረቡ ይህንኑ አንድነት፣ ለነጻነታችንንና መብታችን መከበር መሳኝ ነው የሚል መልእክታቸውን እያስተጋቡ ነው። የአትላንታ፣ የኦጋዴንና የኦሮሞ ማህበረሰብ ተወካዮች ከግንቦት 7 አመራር ጋር ህዝባዊ ስብሰባ አድርገው ለመብታችን መከበር፣ ግፍና ሰቆቃ እንዲያበቃ ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን እንቁም ሲሉ ያስተጋቡት መልእክት በመላው ሃገሪቱ ውስጥ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ግፍና መከራው የመረረውን ዜጋ ሁሉ ስሜት የሚያንጸባርቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ አይነቱን ከጋራ ስቃይ የመጣ የማህበረሰባችንን የመቀራረብ ጥሪ አንደኛው ድርጅት ሌላውን አዘናግቶ ለመመታት የሚደረግ የሴራ ውጤት እንደሆነ አድርገው የሚያቀረቡ ድርጅቶችና ግለሰቦች እያየን ነው። እንደ ግንቦት7 አመለካከት እነዚህ አካላት እንዲህ አይነቱን አቋም መያዝ የቻሉት በአፍሪካችን እየነፈሰ ያለው ነፋስ ህዝብ ባንድ ላይ በግፍ አምራቾች ላይ እንዲነሳ እንጂ የድርጅቶች ሴራ መሳሪያ የሚሆነበትን ሁኔታ የማይጠቁም እንደሆነ ካለማጤን የመጣ ነው ብሎ ያምናል። ይህንን በደንብ ሳያጤኑ፣ በአለንበት ዘመን ከዲሞክራሲ ስርአት ውጭ የሃገር አንድነት ይከበር ይመስል የፖለቲካ ቡድኖችንና ማህበረሰቦችን ከፊሎቹን "የአንድነት ሃይሎች" ከፊሎቹን ደግሞ "የጸረ አንድነት ሃይሎች" በሚል ፍረጃ በሃገራችን ለዴሞክራሲ በአንድነት የሚደረገውን ትግል መከፋፈል ማንን እንደሚጠቅም ለማወቅ ብዙ ምርምር አይጠይቅም።

የችግሮች አደራደርና አቀማመጥ በመፍትሄያቸው አሰጣጥ ላይም የራሱ የሆነ ተጸእኖ እንዳለው መረዳት ተገቢ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ያሉትን ችግሮች በሙሉ ብንደረድራቸው መፍትሄያቸው ከዴሞክራሲ አለመኖር ጋር በቀጥታ ይተሳሰራል። ወያኔ በያዘው መንገድ እንዲነጉድ እድል ከተሰጠው ኢትዮጵያ እንደ ሃገር ህልውናዋ የመቀጠሉ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው። ይህ ግንቦት 7ን በእጅጉ ያሳስበዋል።

ግንቦት 7 ስለአንድነት ብዙ ስለጻፍን፣ ስላወራን፣ ስለዘመርን፣ ስላቅራራን በሃገራችን ላይ ያንዣበበውን የመበታተን አደጋ እናስወግደዋለን ብሎ አያምንም። የሃገራችንን አገራዊ ጥቅምና አገራዊ ደህንነት የሚጎዱ ማለቂያ የሌላቸው ድርጊቶች በወያኔ ሲፈጸሙ ቆይተዋል፤ እየተፈጸሙም ነው። ወያኔ ተወግዶ ሌላ ሃይል ስልጣን ላይ ቢመጣ እንኳን ለሃገራችን ህልውና ዋስትና የሚሰጠን የህዝብ የበላይነት የሰፈነበትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት ስንችል ነው።

ኢትዮጵያ ረሃብ፣ በሽታ፣ መሃይምነት፣ ዘረፋ፣ አፈና ሰቆቃ የተንሰራፋባት ሃገር ናት። የእነዚህ ችግሮች መፍትሄ ዞሮ ዞሮ ህዝብን የሚፈራና ስራው በህዝብ የሚፈተሽ፣ ለህዝብ ተጠያቂ ከሚሆን መንግስታዊ አስተዳደር ምስረታ ጋር ይያዛል። ዲሞክራሲ ከመሰረታዊ ችግሮቻችን ጋር ያለው ትስስር ፍንትው ብሎ የሚታይ ጉዳይ ነው። "በፖለቲካ ድርጅቶች መሃል የሚደረግ የወቅቱ ምክክርና ትብብር ቅድሚያ ለዲሞክራሲ በሚሰጡ ሃይሎች እንጂ ሌላ ነገር ለሚያስቀምጡ ሊሆን አይገባውም" የምንለው ለዚህ ነው። "የኢትዮጵያ ችግር የአንድነት ችግር ነው ወይስ የዴሞክራሲ?" የሚል ጥያቄ ቢቀርብ "ችግራችን የአንድነት ችግር" የሚሉ ብዙዎች ይኖራሉ። ሆኖም በጥሞና ከታሰበ የሃገራችን ችግር የዲሞክራሲ አለመኖር መሆኑን፤ የአንድነት ችግራችን በዲሞክራሲያዊ ስእአት መመስረት በቀላሉ የሚቃለል መሆኑን መረዳት የሚቸግረን አይመስለንም።

ሃሳቦችን ችግር በመፍቻነት በማቅረብ እና ሃሳቦችን ለፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት በመጠቀም መሃል ትልቅ ልዩነት አለው። የሃገር አንድነት ጉዳይ የሚያሳስበው በርካታ ዜጋ አለ በሚል ስሌት የኢትዮጵያን ችግር በአንድነትና በጸረ አንድነት ሃይሎች መሃከል በሚደረግ ትግል እንደሚፈታ አድርጎ ማቅረብ ሃቀኛነት የጎደለው አካሄድ ነው የምንለው ለዚህ ነው። የኢትዮጵያ ችግር ለአንድነት በቆሙና የመገንጠል አላማ ባላቸው ድርጅቶች መሃከል ብቻ የሚያጠነጥን አይደለም። ለዴሞክራሲ በቆሙ የአንድነት ሃይሎችና ለዴሞክራሲ ባልቆሙ የአንድነት ሃይሎች መሃከል ያለው ችግርም በቀላሉ መታየት የለበትም። ጠባብ የቡድን ፍላጎት ለማራመድ ሲል ለዜጎችና ለማህበረሰቦች ነጻነት የሚከለክል የአንድነት ቡድን ለጠባብ ፍላጎትና ጥቅም ሲል የመገንጠል አላማ የሚያራግብ ቡድን ከሚፈጥረው ችግር ያልተናነሰ ችግር ሊፈጥር ይችላል።

በተለይ ባሁኑ ሰአት የሀገራችን ህዝብ በሙሉ በጸረ አምባገነንነት ትግል ዙሪያ ለመቆም ዝግጅት እያደረገ ነው። ባለፉት ሃያ አመታት አንዱ ማህበረሰብ ሌላውን እንዲጠራጠርና እንዲፈራ ያደረጉ በርካታ የጭካኔ ተግባራትና የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ስራዎች ተሰርተዋል። የህዝባዊ አንድነት ጉዳይ ገና መሄድ እንደጀመረ ህጻን ወፌ ቆመች እየተባለ የሚበረታታ እንጂ አንዳንድ ጸረ_ወያኔ ነን የሚሉ ቡድኖች እንደሚያደረጉት የጥቃትና የዘለፋ ኢላማ ሊሆን አይገባውም። ወያኔ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ከፈጠረው አደጋ በላይ በአካባባዊና በሀገራዊ ሁኔታዎች እየተገፉ በጋራ ለመስራት ጥረት የሚያደርጉ የማህበረባችን አባላት በምን ስሌት ነው የሃገራችን አንድነት የከፋ አደጋ ተደርገው የሚታዩት። ወያኔን የሚያህል ጸረ-አንድነት ሃይል አስቀምጦ፣ በአንድነት ለመስራት እጆቻቸውን እየዘረጉ ያሉ የማህበረሳባችንን አባላት አታስጠጉ የሚል መልእክት መነሻው ምንድነው? ችግር ለመፍታት የሚደረግ ነፍስ ቡርቦራና ርካሽ የፕሮፓጋንዳ ቀቢጻዊ እርካታ ለማግኘት የሚሰሩ ስራዎች ትልቅ ልዩነት አላቸው። የፕሮፓጋንዳ አዋራ ከረገፈ በኋላ የሚቀረው ያው እፍ ብንል የማይጠፋው እውነታ ነው። ያ እውነታ የኢትዮጵያ ችግር በዴሞክራሲያዊ ሃይሎችና በጸረ_ዴሞክራሲ ሃይሎች መካከል በሚደረግ ትግል ብቻ የሚፈታ መሆኑ ነው። የአንድነቱም አደጋ ምላሽ የሚያገኘው በዚሁ በዲሞክራሲ ማእቀፍ ውስጥ ብቻ ነው።

ያለዜጎች አንድነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው ጸረ -አምባገነናዊ ትግል የትም እንደማይደረስ ለሁሉም ዜጎች ግልጽ በሆነበት ባሁኑ ወቅት የተለያዩ ፕሮግራሞች ያሏቸው ድርጅቶች ሊያነሱ የሚገባው ጥያቄ እንዴት አድርገው ይህን የህዝብ የትግል አንድነትና ስሜት ማበረታት ይችላሉ የሚል ነው። የወቅቱ በድርጅቶች መሃከል የሚደረግ ውይይት እንዲህ አይነቱን ጉዳይ በዋንኛት መነጋገሪያው ሊያደረገው ይገባል የሚል እምነት አለን።

## 6. ለአጋርነት እንጂ ለመሪነት ያልበቃ ተቃዋሚ

የፖለቲካ ድርጅቶች አንድ ህዝብ ከደረሰበት ንቃተ ህሊና ላይ የተመረኮዘ እቅድ ያወጣሉ እንጂ እነሱ ባንድ ወቅት ይዘውትና ለመልቀቅ ወደማይፈልጉት አመለካከትና ተግባር ህዝብን መጎተት የለባቸውም። ዘመኑ ህዝብ ራሱን በራሱ አደራጅቶ የራሱ ነጻ አውጭ መሆን የሚችለባቸውን አዲስ የነጻነት የትግል ሂደት የተከፈተበት ዘመን መሆኑን ሁላችንም መረዳት አለብን። "አንድ የተማከለ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ግንባር ፈጥረው የለውጥ ወኪሎች ካልሆኑ በአንድ ሃገር ላይ ለውጥ መምጣት አይቻልም" የሚለው ነባር አመለካከት ክፉኛ የተመታበት ዘመን ላይ ደርሰናል። በፖለቲካ ልሂቁና በህዝብ መካከል የነበረው ግንኙነት በሞግዚትና በህጻን መሃከል እንደሆነ ተደርጎ ሲሰራበትና ለተከታታይ አምባገነናዊ ስርአቶች መመስረት ምክንያት የነበረው እንከን የተነቀለበት የታሪክ ምእራፍ ላይ ነን። በመቶዎችና በሽዎች በሚቆጠሩና ህዝብ ራሱ በፈጠራቸው ቡድኖች የሚመሩ እንቅስቃሴዎች፣ ለዘመናት የፖለቲካ ድርጅቶች ምንም ሊያደረጓቸው ያልቿላቸውን አምባገነኖች ሲያንበረክኩ አይተናል። ለነጻነት መምጣት ለሚጣደፍና አላማው ህዝብ የነጻነትና የስልጣን ባለቤት እንዲሆን ፍላጎት ላለው ድርጅት ከዚህ በላይ ሊያስቀና የሚችል ኩነት ከየትም ሊመጣ አይችልም።

(ክፍል 4 ሳምንት ይቀጥላል)

## መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያዊያንን በሌላ ዙር ጦርነት ውስጥ ለመዝፈቅ እየተንቀሳቀሰ ነው፤ 200 ታንኮችን በቀድሞ ጊዜ የሶቭት ህብረት ግዛት ከነበረቺው ዩክሬን እንደገዛ ታወቀ

ህዝብን በጉልበትና በጠመንጃ አፈሙዝ አምበርክኬ በስልጣን ላይ እቆያለሁ ብሎ የሚያልመው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከዩክሬይን መንግስት በአንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሁለት መቶ ታንኮችን መግዛቱን ኪቭ ፖስት በመባል የሚታወቀው የዩክሬይን ዜና አገልግሎት ይፋ አደረገ።

እንደ ኪቭ ፖስት ዘገባ አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከዩክሬይን የገዛቸው ሁለት መቶ ታንኮች እጅግ በጣም ዉድና ዘመናዊ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን የዘረኛው አገዛዝ የፈጸመው ግዢ በዩክሬይን ባለፉት አስራ አምስት አመታት ውስጥ ከተፈጸሙት ስምንት የሚሆኑ የጦር መሳሪያ ሽያጮች አንዱ መሆኑ ታውቋል።

ይህን ዜና ተከትሎ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው በውጪ ሃገር ነዋሪ የሆኑ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ በሰጡት አስተያየት ወያኔ ኢትዮጵያዊያንን በጉልበት እስከዘለአለሙ የመግዛት ህልሙን እውን ለማድረግ የማይቆፍረው ጉድጓድ እንደሌለ ጠቅሰዉ በተለይም ይህ የታንክ ግዢ አንዴ ከኤርትራ ጋር ሌላ ጊዜ ደግሞ ከግብጽ ጋር ጦርነት እገጥማለሁ በማለት የህዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለመቀየር ሲሞክር የሰነበተው ወያኔ ምናልባትም ጎረቤት ኤርትራን በመተንኮስና ጦርነት ውስጥ በመክተት የህዝቡን ለለውጥ የመነሳሳት ስሜት ለማዳፈን ሊጠቀምበት እንደሚችል ግምታቸውን ገልጸዋል፤ ፤ አያይዘውም ኢትዮጵያ በድህነትና በረሀብ የምትታወቅ ሃገር ሆና እያለ ለጦር መሳሪያ ግዢ ይህን ያህል ገንዘብ መፍሰሱ የዘረኛውን አገዛዝ የጥፋት ተልእኮ አጉልቶ ከማሳየት ውጪ የሚፈይደው ነገር አይኖርም ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቀደም ሲል ከእስራኤል ሃገር በእንግሊዝኛ አጠራሩ አን ማንድ ወይም ሰው አልባ የጦር አውሮፕላን መግዛቱ ይታወሳል።

## አሜሪካ ስለዲሞክራሲ እየደሰኮሩ የህዝባቸውን ስቃይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

"በሰሜን አፍሪቃ የተካሄዱት እንቅስቃሴዎች በተቀረው የአህጉሪቱ ክፍሎች ያሉትን ህዝቦች በማነቃቃት ያለዲሞክራሲ ህዝባቸውን የሚገዙትን አፋኝ መንግስታት ፈተና ላይ ጥሏል ያሉት ክሊንተን ፤ ህዝብ የሚፈልገውን አይነት ለውጥ ለማምጣትና ሠላምና መረጋጋትን ለማስፈን በቂ ጊዜና እድል ሰጥቷቸዋል" ይህን ዕድል ተጠቅሞ ተግባራዊ ለውጥ አለማድረግ ግን በሌሎች የሰሜን አፍርካ አገሮች የሆነውን አደጋ ይጋብዛል በማለት አስጠንቅቀዋል። "ለዚህ ታሪካዊ ተግባር ቁሙ፤ የህዝቦቻችሁን ፍላጎት ለማስከበር የሚችል እዉነተኛ መንገድ ተከትላችሁ የአመራር ብቃታችሁን አሳዩ፡ በማለት ጥሪ ያደረጉት የአሜሪካ ወጪ ጉዳይ ምንስትር፡ ይህን ካልፈፀማችሁ በተሳሳተ የታሪክ አቅጣጫ ላይ መሆናችሁን ጊዜ ያረጋግጠዋል" በማለት በቱኒዚያ የፈነዳውና የግብጽን አምባገነን ገርስሦ ወደ ሊቢያና ሌሎች አረብ አገሮች እንደሰደድ እሳት የተዛመተው ህዝባዊ አመጽ ወደሌሎች የመዝለቁን አይቀሬነት ተንብየዋል።

ክሊንተን በዚሁ ንግግራቸዉ በአሜሪካና በአፍሪቃ አገሮች መካከል ያለዉ የንግድ ግንኙነት እንዲጠናከር ከማሳሰባቸዉም በላይ አገራቸዉ በምግብና በጤና ረገድ የምታደርገዉ እርዳታ እንደሚቀጥል ገልፀዋል።

በሊቢያ እየተካሄደ ያለውን ህዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴ አስመልክቶ፤ የአፍሪካ መሪዎች በሙሉ ከሊቢያዉ አምባገነን መሪ ሙአመር ጋዳፊ ጋር ያላቸዉን ግንኙነትና ወዳጅነት አቋረጥው ለለውጥ አራማጁ ሃይል እውቅና እንዲሰጡ ጥሪ ያደረጉት ክሊነትን ፤ጋዳፊ ከብዙዎቹ ጋር የረዢም ጊዜ የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዳላቸዉና የአፍሪቃ ህብረትን ጨምሮ ብዙ የአፍሪቃ አገራትን በፋይናንስ ሲረዱ እንደነበር የሚታወቅ ቢሆንም በስልጣን ላይ የመቆየት ጊዜያቸዉ ካለፈ የቆየ በመሆኑ የአፍሪካ መሪዎች በሊቢያ የተኩስ ማቆም እንዲኖር ጋዳፊ ስልጣን እንዲለቁ አሁኑኑ መጠየቅ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ከዚህ ሌላ የህብረቱ አገሮች የጋዳፊን ኤምባሲዎች እንዲዘጉና ዲፕሎማቶቻቸዉን ከአገር እንዲያባርሩ፡ በምትኩ በአማፅያኑ ለተቋቋመዉ ብሄራዊ ምክር ቤት እዉቅና እንዲሰጡ ጠይቀዋል። ይህን ስትፈፅሙ በሊቢያ የሚካሄደዉን ነገር ለመለወጥ ያስችላል፤ ህዝቡ ወደ ሰላማዊ ኑሮዉ ይመለሳል፤ ህገመንግስት ጽፎ፤ አገሩን በአዲስ መልክ መገንባት ይጀምራል በማለት ገልፀዋል።

ከአፍሪካ ህብረት ንግግራቸው ቦኋላ መለስ ዜናዊን ለአንድ ሰ ዓት በጽቤቱ ያናገሩት ምስ ሂላሪ ክሊንተን፤ ከሰሃራ በታች የሚገኙ አብዛኛዎቹ አገሮች ለዜጎች መብቶች እውቅና የሰጡና ስለመልካም አስተዳደር ውብ የሆነ ድንጋጌ ያላቸው ህገመንግሥት ባለቤቶች ቢሆኑም ዋናውና ትልቁ እንቅፋት የሆነው በወረቅት ላይ የሰፈረውን ህገመንግሥታዊ መብት በተግባር ለመተርጎም ፍቃደኝነት መጥፋቱ ነው በማለት ዲፕሎማሲያዊ በሆነ ቋንቋ መለስ ዜናዊ ስለ ዲሞክራሲ የሚያደርገው የአመታት ድስኩር አገራቸው አሜሪካንን ምን ያህል እንዳሰለቸና ተስፋ እንዳስቆረጠ ተናግረው ማለፋቸውን ለማወቅ ተችሎአል። መለስ ዜናዊ በበኩሉ ኢትዮጵያ ሽብርተንነትን ለመዋጋት እየፈጸመቺው ካለው ጅብዱ በተጨማሪ የአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ለማስከበር አሜሪካ ይጠቅማል ወደምትለው የትኛውም ስፍራ ወታደሮቿን ለማሰማራት ፍቃደኛና ዝግጁ መሆኑን እንደገለጸ ታውቆአል።

የመለስ ዜናዊ ውጪ ጉዳይ መሥሪያቤት አፈቀላጠ ሙፍቲህ ሙሳ ምንስትሯ ሂላሪ ክሊንተን ከመለስ ዜናዊ ጋር ባደረጉት ውይይት ስለ ዲሞክራሲ ያነሱት ሃሳብ የለም ሲል በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማሪኛው ክፍል ማስተባበሪያ ሰጥቶአል። እንደ ቃለ አቀባዩ ሙፍቲህ ሙሳ ክሊንተን ስለዲሞክራሲ ሳያነሱ ቀርተው እንኳ ከሆነ ይህ በራሱ የሚያመለክተው የኦባማ አስተዳደር በመለስ ዜናዊ የዲሞክራሲ ሥር ዓት ግንባታ ባዶ ቃል የተሰላቸና አይቀሬው ህዝባዊ አመጽ ደርሶ ከመንበሩ እስኪፈነግለው በሌሎች ያካባቢው ጉዳዮች ብቻ አብሮ ለመስራት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን እንደሚያሳይ የፖለቲካ አዋቂዎች ይናገራሉ።

ሂላሪ ክሊንተን አዲስ አበባ ሲገቡ አውሮፕላን ጣቢያ ደርሶ አቀባበል ያደረገላቸው የህወሃት ተለጣፊ ድርጅት አባል የሆነውና ለመለስ ዜናዊ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ማረጋገጫነት ሽፋን የተመረጠው ሃይለማሪያም ደሳለኝ እንደሆነ ይፋ የሆነው ዜና ያስረዳል። ሃይለማሪያም ደሳለኝ በምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት በፈላጭ ቆራጩ መለስ ዜናዊ ሥር በውጪ ጉዳይ ሚንስትርነት ስልጣኑ ደግሞ በሌላኛው የትግራይ ተወላጅ ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ሞግዚትነት ስር የሚንቀሳቀስ አሻንጉሊት እንደሆነ የወያኔን የሥልጣን ሰንሰለት በቅርበት የሚያውቁ ሰዎች እየመሰከሩ ነው።

## የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የምግብ ድጋፍና የእንክብካቤ አገልግሎት መስጫ ተዘጋጅቶ አለመሠራጨቱን በሪፖርታቸው የገለጹት አቶ ገመቹ፣ ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውና የተመደበው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ አልዋለም ብለዋል።

በኤች አይቪ ቫይረስ የተያዙ በርካታ ወገኖች መድህኒትና በቂ ምግብ ማግኘት ተስኗቸው እንደ ቅጠል እየረገፉ ባለበት ወቅት በኤይድስ ህመምተኞች ስም የመጣውን ብዛት ያለዉ ገንዘብ ለተለያዩ ጉዳዮች ውሏል በሚል ሰበብ የሚደረገው ዝርፊያ አስደንጋጭ መሆኑን በቅርቡ ይህን ሁኔታ በመቃወም አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ አንድ በተስፋ ድርጅት ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሰው ለኢሳት ምንጭ መናገራቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን በትናንትና የዜና ዘገባው ይፋ አድርጓል።

ለኢሳት ዘገባውን የሰጡት እኚህ ውስጥ አዋቂ ለኤቺ አይቪ ህመመተኞች የሚሰጠው የገንዘብ እርዳታ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር ቀጭን ትእዛዝ የምትሰጠው የሙስናዋ ልዕልት አዜብ መስፍን መሆኗን ብዙዎች ያሰምሩበታል።

ህወሃት የጫካ ትግል ያደርግ በነበረበት ወቅት ከመለስ ዜናዊ ጋር በፍቅር ከመወደቋ በፊት ለህወሃት መሪዎች ምግብ አብሳይ የነበረችው አዜብ መስፍን ወይም አስቴር ጎላ በቅርቡ አንድ የስፔን ጋዜጣ ይፋ እንዳደረገው በአፍሪካ አባካኝ ከሚባሉት የአምባገነን ሚስቶች ተርታ የምትመደብ ሴት እንደሆነችና ባለቤቷ መለስ ከ35 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት በውጭ አገር ባንኮች እንዳስቀመጠ መዘገቡ ይታወሳል።

## በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በ2002 የበጀት አመት .ከአንድ ነጥብ . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ምንም የሚደንቅ አይደለም። ስለሙስና ካወራንና ሙስናንም ለመቆጣጠር ከተፈለገ ደግሞ መጀመር ያለብን ከራሱ ከመለስ ዜናዊና ከባለቤቱ ከአዜብ መስፍን መሆን ነበረበት ብለዋል።

እንደ ሪፖርተር ዘገባ ሪፖርቱ የፓርላማ አባላትን ለምን እንዳስጨበጨበ እኔ አልገባኝም፥ ምናልባት ኦዲተር መስሪያ ቤቱ ቁልፍ የሚባሉ ባለስልጣናትንና የወያኔ ቁንጮዎችን የማይነካ ሪፖርት በማቅረቡና በዚህም አጋጣሚ ሊመቱ የተፈለጉ ባለስልጣናት ካሉ የዚያ ደስታ መግለጫ ሊሆን ይችላል በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

## የዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ ባለስልጣን ተስፋየ ሃቢሶ በሌላ ተጨማሪ የአእምሮ ፈጠራ ስርቆት ተግባር መሰማራቱ ተገለጸ

ቀደም ብሎ በዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በአምባሳደር ማእረግ በዩጋንዳና በደቡብ አፍሪቃ ተቀምጦ የነበረው ተስፋዬ ሃቢሶ ዶክተር ኮሊን ዳርች የተባሉ በእንግሊዝ ሃገር የተወለዱ ደቡብ አፍሪቃዊ ምሁር በኢትዮጵያ ላይ ጥናት በማድረግ ያወጡትን የምርምር ውጤት ጽሁፍ አንድም ቃል ሳይቀይር እንዳለ የራሱ የምርምር ውጤት አድርጎ በተለያዩ ድህረ ገጾች ላይ ማሳተሙን ጋዜጠኛ አበበ ገላው ማጋለጡን ቀደም ብለን የዘገብን ሲሆን በትላንትናው እለት ኢትዮ ሚድያ በመባል የሚታወቀው የመረጃ አውታር ተስፋየ ሃቢሶ በተመሳሳይ መልክ ሌላ የ አእምሮ ፈጠራ ንብረት ስርቆት መፈጸሙን አጋልጧል።

እንደ ኢትዮ ሚድያ ዘገባ ተስፋየ ሃቢሶ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር 2009 ዓም ላይ በጋና የተጻፈ የጥናት ውጤትን የራሱ የስራ ውጤት እንደሆነ አድርጎ ማቅረቡንና ያው ሶፊዝም የተባለ ጋናዊ በእንግሊዝኛ "The Rise of Incivility In Our Public Discourse." በሚል ርእስ የጻፈውን ጽሁፍ ከስድስት አመታት በኋላ የራሱ አእምሮ ፈጠራ ውጤት አድርጎ ማቅረቡን አጋልጡአል። ባለፈዉ ዐርብ ማምሻዉን ደግሞ አንድ ሌላ ተመራማሪ የአቶ ተስፋየዬ ሃቢሶን ሌላ የስርቆት ጽሁፍ ፈልፍሎ በማዉጣት አቶ ተስፋዬ የሰዉን የሌሎችን የፈጠራ ስራ ዬኔ ነዉ ብሎ ማዉጣት እንጂ በራሱ የሚሰራዉ ምንም ነገር እንደሌለ በተግባር አሳይቷል። መለስ ዜናዊና በዙሪያዉ የተኮለኮሉ ምናምንቴዎች የማይሰርቁት ምንም ነገር እንደሌለ የተስፋዬ ሃቢሶ ነዉር ተግባር ምስክር ነዉ።

ተስፋየ ሃቢሶ የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ኣጫፋሪና ደጋፊ በሆኑት እንደ አይጋ ፎረም፣ ኢትዮጵያ ፈርስት፣ እንዲሁም ትግራይ ኦን ላይን ላይ የተለያዩ ጽሁፎችን በማውጣት የሚታወቅ ሲሆን፣ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በ 2002 በተደረገው ምርጫ 99.6 በመቶ በሆነ ድምጽ ህዝብ መርጦኛል ብሎ ሲያውጅ የምርጫ ውጤቱ ትክክል አለመሆኑን የውጭ ታዛቢዎች እየመሰከሩ ባለበት ሁኔታ ምርጫው ትክክለኛና ፍትሃዊ ነበር ብሎ ሲደሰኩር እንደነበር ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፤ 7175፤ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org